# እንዴት ዛሬም ፤ የገደለሽ ይብላ?

የሐገራችን የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንመለከት ዘወትር በጸረ ኢትዮጵያዊነት የተሰለፉ ከውጭና ከውስጥ ጠላት ጋር በማበርና በመመሳጠር አገሩንና ሕዝቡን የበደለ ፤ የወጋና ያደማ ሲሾም ሲሸለም በአንጻሩ ደግሞ ለሐገሩና ለወገኑ የቆመው ሲሳደድ ፤ ሲታሰር ፤ ሲገደል የኖረባት አገር እንደሆነችና ዛሬም በዚያው ሁኔታ እየቀጠለች ያለች አገር መሆኗ ለሁላችንም ግልጽ ነው ።

አለመታደል ነው መሰለኝ አገሬንና ወገኔን አላስነካም ፤ አላስደፍርም ብሎ የታገለ ሁሉ ባለበት ዘመን ለሱ የሚወግነውና የሚከራከረው ክፍል እጅግ በጣም ጥቂቱ ነው ። ሆኖም ግን ያ ዘመን ካለፈ በኋላ ተወቃሽ ፤ ተነቃሽ የነበረውን አገር ወዳድ አርበኛ ህይወቱ ካለፈ ከዘመናት ከተቆጠሩ በኋላ እንደገና በአርበኝነትና በአገር ወዳድነት ሲነሳና ሲወደስ ፤ ሲሞገስ ይሰማል ።

ታዲያ ሰው እየሰራ ባለበት ዘመን ስራውን ማበረታታትና ማወደስ ሲገባ ውንጀላውና ኩነናው ከምን የመጣ ነው? ለአገርና ለወገን ተቆርቁሮ በሚሰራበት ወቅት መወገዝ ፤ መሰደድ ፤ መታሰር ፤ መገደል ያለበት ለምን ይሆን? ሥራ በሚሰራበት በህይወት ዘመኑ ኮንኖ ካለፈ በኋላ ስሙን መጥራትና ማወደሱ የሚያከናውነው ተግባር ምንድነው?

ካለፈው ስህተታችን መማር ተስኖን ዛሬም ለአገርና ለወገን የቆመ ሁሉ ሲወገዝ ፤ አይንህ ላፈር ሲባል መስማትና ማየት እውነት እቺ አገር ከልብ የሚወዷትና የሚቆረቆሩላት የነደሩ የቀደምት አርበኛ አባቶቻችን ከወገንና ከአገር በደረሰባቸው በደል የተነሳ ሰው አይውጣልሽ ብለው እረግመዋት  አልፈው ይሆን? ዛሬም እውነተኛ ታጋዮች ተወግዘው ለጠላት ካጎበደደ ፤ ከባዕድ ከሰገደ ፤ ከአጥፊያችንና ከገዳያችን ፍቅርን የምናሳየውና እውነተኛ ታጋዩን የምናወግዘው?

አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ አገር ባፈራቸው የእንግዴ ልጆች ፤ ተምቾች ተወጥራ ተይዛ መከራዋን እየቆጠረች ትገኛለች ። ቀደም ባሉ ኢትዮጵያን ባስተዳደሩ መንግሥታት ጽናትና አገር ወዳድነት የተነሳ የምዝበራና የማፍረስ በሩ ተዘግቶባቸው የነብሩ ጠላቶቿ ሁሉ ቀንና ጊዜን ሲጠብቁ ቆይተው ፤ ዛሬ የኢትዮጵያዊነት አንዲት ጠብታ ደም በውስጣቸው የማይፈስ የባዕዳን ታማኝ ሎሌዎች በለስ ቀንቷቸው የስልጣን ባለቤት በመሆናቸው የተነሳ አገራችን ለውጭ ጠላት በሯን ከፍተው በማስተናገድ ፤ ካንደም ለሁሌም ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳትኖር ፤ ለማጥፋት ፤ ቀን ከሌት ደፋ ቀና እያሉ ካለመታከት በሚሰሩበት ወቅት ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ይህ እንዳይፈጸም ነቅተውና ቆርጠው በመታገል ላይ ያሉትን የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደ አገር ጠላት አድርጎ ፈርጆ እውነተኛውን የአገር ጠላት ደግሞ እንደ አገር ወዳጅ ፤ አገር አድን  አድርጎ አገርን ለማጥፋት በሚደረገው እርብርቦሽ ላይ ሲራኮቱ መመልከት ኪታከፍ የማይችል ጉዳይ እየሆነ እንደሆነ ማስገንዘብ የግድ ይላል ፤ አንዳንዶቹ ባለማወቅ ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ሆን ብለውና አውቀው ፤ ሕዝብን በማወናበድ እውነተኛ ታጋዮችን በማስመታትና በመምታት እንደ ዘመን አመጣሽ ፋሽን ተይዞ ላገር ጥፋት ዱላ በማቀበል ትብብራቸውን ተያይዘውት ይታያል ።

"አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ
የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ"

ተብሎ የተንጎራጎረላት ዛሬም እየተደገመ መሆኑ እጅግ በጣም ያሳዝነኛል ።

ዛሬ አገራችንን አምስትና ስድስት ቦታ እንድትከፈል ተደግሶላት ፤ ስልጣን ላይ ባለው የትግሬ መንሥስት አጋዥነትና በአጎራባች የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ አገሮች እንደ ግብጽና ሳውዲ አረቢያን የመሳሰሉት የአገራችንን ጥፋት ለሚመኙ አገራችንን ለማፍረስ ተግተው እየሰሩ ባሉበት በአሁኑ ወቅት እኛም የገዛ አገራችንን እንድትፈራርስ አስፈላጊ የሆነውን መሳሪያ በማቀበል እየተባበርን አገርን ከውድቀት ልናድን ነው እያልን እራሳችንን ማታለል ከጀመርን ውለን አድረናል ። አገርን ማዳን ካፍራሽና ከገንጣይ ጋር ተባብሮ መስራት ከሆነ ፤ አገር ማዳን አገርን ኪበትን ከተዘጋጀ መዋቅር ጋር በማጎብደድ ከሆነ ይህ አይነቱ አገር ማዳን ጨዋታ ለምን ባፍንጫዬ አይወጣም ፡ ይሄማ ተብሎ የሚጠራው ባንዳነት ነው ፤ ምናልባት ትርጉሙ ያልገባው ካለ ።

በስልጣን ላይ ያለውን የወያኔን አገዛዝ ደጋፊዎች ከጥቅሙ ተካፋይ ከሆኑት እጅግ በጣም አነስተኛ ከሆኑ ጸረ ሕዝቦች በስተቀር 99 በመቶ የሚሆነው ሕዝባችን ለአገዛዙ ከፍተኛ የሆነ ጥላቻ እንዳለው ለሁላችንም ግልስ ነው ። ነገር ግን የምዕራባውያን ጥቅም አስጠባቂና ተላላኪ የሆነው ወያኔ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የሚፈጽመው ግፍና በደል ለምዕራባውያኑ ስውርና የማይታይ እንዲሆን አድርጎታል ። ምዕራባውያንም በመሰረቱ ለጥቁር ሕዝብ ምንም አይነት ደንታ እንደሌላቸውና እንዲያውም ከጥቁሩ ሕዝብ መካከል እንደ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ የሚጠሉትና የሚፈሩት እንደሌለ የአደባባይ ሚስጥር ነው ። ስለሆነም የኢትዮጵያ መበታተን ለነሱ ደስታ እንጂ ሀዘናቸው አይሆንም ። ጥቅም ያገኙ እንደሆን እንጂ ከኛ መበታተንና መጥፋት ምንም የሚቀርባቸው ነገር አይኖርም ። በጥቁር ሕዝብ ውድቀት ቢደሰቱ እንጂ አይከፋቸውም ። ለጥቁሩ እርህራሄና ቀና አመለካከት ይኖራቸዋል ማለት እራስን ማታለል ካልሆነ በቀር ሌላ ሥም ልሰጠው አልችልም ።

ነጭ ለጥቁር አስቦ አያውቅም ፤ ለወደፊትም አያስብም ፤ የሚያስበው ለራሱ ብቻ እንደሆነ ማወቅ የግድ ይላል ። ዚምባዌን እንደምሳሌ ብንወስድ ሙጋቤ በነጭ ተይዞ የነበረውን የአገሩን ሰፊ የእርሻ መሬት ከነጩ ወስዶ ለባለንብረቱ ለጥቁሩ በመስጠቱ እንዴት ጥርስ እንደተነከሰበት ሁላችንም የምናውቀው ነው ፤ ሙጋቤ በመላው ምዕራባውያን የተጠላ የሆነው በእውነት ሙጋቤ በአገሩ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ጭቆና አሳሳስቧቸው ለጥቁሩ የዚምባዌ ሕዝብ ተጨንቀውለትና አስበውለት ሳይሆን እንዴት ቢንቀን ነጩን ገበሬ መሬቱን ቀምቶ ለጥቁሩ ሰጠ ከሚል ካራሳቸው ካላቸው የትልቅነት ግምት እንደሆነ ልንስተው አይገባም ። ስለሆነም ዛሬ አንድ የሙጋቤ ወታደር አንድን ሲቪሊያንን ገፋ ወይም በጥፊ መታ ተብሎ የምዕራቡ ሚዲያ አዛኝ ቅቤ አንጓች ይሆናል ፤ ከአገሬው ሰው በላይ ኪያለቅሱም ሲዳዳቸው ይታያል ፤ "እቺ እቺን ለኛ ጥሬ ለጌኛ" ይላል ያራዳ ልጅ ሲተርትና ሲቀልድ ጨዋታው ሌላ ነው ወገኖቼ ። ከነጩ ነጥቆ ለጥቁሩ የሰጠው መሬት ዛሬ የተሻለ ምርት ይሰጣል ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላልል ፤ እሱ ግን እራሱን ችሎ ሰፊ ትንታኔ ይጠይቃል ፤ ያም ሆኖ ግን በነጩ ባለቤትነት ዘመን እንደነበረው ለምን ውጤታማ አልሆነም ለሚለው መልስ ትንታኔው ሰፊ ነው ባጭሩ ግን ክውስጥ አስተዳደር ይልቅ የነጩ የተወሳሰበ ተንኮል ስላለብት ወደዚያ አልገባም ። ወደ አገራችን ስንመለስ የመለስ አጋዚ ጦር በመላ አገሪቱ ውስጥ በቀን ቢያንስ አስር ሰው ሳይገድል ፤ ሳያንገላታ ፤ ሳያስር ፤ ፍርድ ሳይዛባ አይውልም ፤ አያድርም ፤ የነኚህ ጉዶች ሚዲያ ግን የሚዘክርልን የመለስ አስተዳደር እንዴት ጽረ ሕዝብ እንደሆነ ሳይሆን በተቃራኒው ወያኔ ከአፍሪካ ለአብነት የሚጠቀስ እጹብ ድንቅ የሆነ አስተዳደር እንደሆነ ነው ፤ ኢኮኖሚው ከሕንድና ከቻይና በላይ 11 በመቶ ለተከታታይ 10 ዓመት እያደገ እንደመጣ ሲነግሩን የኛ ቤተሰቦች ግን የሚነግሩን የሚበሉት የሚቀምሱት እንዳጡ ፤ ስራ አጥነቱ በዓለም ተወዳዳሪነት እንደሌለው ፤ በርሃብ አለንጋ የሚጠበሰውና የሚረግፈው ሕዝብ ቁጥር ስፍር እንደሌለው ነው ። ታዲያ ይህ ሁሉ እውነታ እያለ የግልብጡን የሚነግሩን እነዚሁ ጉደኞች ፤ ተላላኪያቸው ወያኔዎችና ፤ ጀሌዎቻቸው ካልሆኑ በቀር ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም ። ስለሆነም እነ ነጮ እዚያው በጠበላቸው እንጂ በኛ ጉዳይ ገብተው ባይፈተፍቱ ይመረጣል ።

የነጩ ህብረተሰብ ስለኛ ስለጥቁሩ ሕዝብ ያላቸውን እውነተኛ ገጽታ ይህንን ያክል ካልኩ በኋላ ወደተነሳሁበት ቁም ነገር ልመልሳችሁ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሁላችንም ወያኔ የአገርና የሕዝብ  ጠላት መሆኑን በተመለከተ አንድ አይነት አመለካከት አለን ብዬ ለማመን እፈልጋለሁ ፤  ነገር ግን ሁሉም የተቃዋሚ ድርጅቶች በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ያላቸው አመለካከት ላይ ስንደርስ ነው ነገር ሁሉ ዝብርቅርቁ የሚወጣው ፤ አገር ወዳድ መስለው አገርን ለጥፋትና ለአደጋ እየጋበዙ ያሉትን እንደ ጀግና አጨብጭበን በመቀበል ፤ ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ ከንቱ ውዳሴ እየሰጠን አሳብጠናቸው በአንፃሩ ግን አለአንዳች ማወላወል የኢትዮጵያን ህልውና ጥያቄ ውስጥ አላስገባም ብሎ የሚታገለውን ከወያኔ ባልተናነሰ አንዳንዴም በባሰ ሁኔታ ሲወገዝና ሲነቀፍ መስማቱ እውነትም "የገደለሽ በላ" የሚለውን ታሪካዊ አሳዛኝ ሁኔታ ለመድገም ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለን ያሳያል ።

አሁን በስልጣን ላይ ያለው የጠባብ ብሄረተኛው አገዛዝ ለሐገርም ለሕዝብም ጠላት መሆኑ ባያጠያይቅም ነገር ግን ስልጣን ያልያዙ በየጫካውና በየሸለቆው የሁላችንም ጠላት የሆነውን የወያኔን አገዛዝ እየወጉ ያሉ እንደ "ኦብነግና ኦነግን" የመሳሰሉ ታጣቂዎች የነሱስ የአገር ጠላትነታቸው እንዴት አልታይ አለን? ጠላትነታቸው በወያኔ ሚዛን የሚለካ ባይሆንም ቅሉ ዞሮ ዞሮ ግን ያው እንደ ወያኔ ኢትዮጵያን የሚጠሉ ፤ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አናውቅም የሚሉ ፤ እንደ ወያኔ ኢትዮጵያ ተሸንሽና አንሳ ፤ ከስማ ፤ እንድትጠፋ የሚማስኑ ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች መሆናቸው ለማናችንም የተሰወረ ሊሆን ባልተገባ ነበር ።

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ አንዱና በጣም አሳዛኙ ትርኢት እየተፈጸመ ያለው "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" የሚለውን ከንቱ ሆያሆዬ ሊተገብሩ ጎንበስ ቀና የሚባልልንና የኛዎቹ ተቃዋሚ ድርጅቶች ፤ ደጋፊዎቻቸው ፤ የነሱ ቋሚ ተጠሪ የሆኑ ሚዲያዎች ፤ የኦብነግ ፤ የኦነግ ፤ ተቆርቋሪና አራጋቢ በመሆን ሽር ጉድ እየተባለ አገር እንዲፈርስ ያቅማቸውን እየደከሙ እውነተኛውን ኢትዮጵያዊ እየመቱ ፤ ነገር ግን ለኢትዮጵያ እየታገልን ነው የሚሉን ። ጎበዝ ዛሬ በየትኛውም ሚዲያ ብትሄዱ ተቃዋሚውን ድርጅት እንደግፋለን የሚሉ የኛዎቹን ደንባሮች ጨምሮ  የምዕራቡም ሆነ የአረቦቹ ቱልቱላ ይህንኑ ሲያራግብና ሲያናፍስ ነው የምናየው ። እንደ እውነቱ ከሆነ አንዲትን ደሃ አገርን ለማጥፋት የሚደረገውን ርብርቦሽ ስመለከት ልቤ ክፉኛ ይደማል ።

ወያኔ ከኦብነግና ከኦነግ ጋር የሚያደርገው ጦርነት ኢትዮጵያ እንዳትቆራረስ ለመጠበቅ ነው ወይ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ፤ መልሱ ግን አይደለም ነው ። መልሱ ደም ማፍሰስ ስለሚወድና እሱም እራሱን እንደ ቅኝ ገዥ ስለሚመለከት የሚወጋቸውም ግንጠላን ሳይሆን የብዝበዛ ምንጭ አድርጎ ስለሚመለከታቸው ኪሱ እንዳይጎል እንጂ የኢትዮጵያን አንድነትን ፈልጎ እንዳልሆነ ለማንም ግልጽ ነው ። ሆኖም ግን ወያኔ በነዚህ ሁለት የግንጠላ ቡድኖች ላይ አደረሰ እየተባለ የሚዘገበው ግን ሁሉም እውነት እንዳልሆነ ልንመረምርና ልናጤን ይገባናል ፤ ወያኔ ጥንት ደደቢት በነበረበት ወቅት የደርግን አገዛዝ በውጪው ህብረተሰብ ለማሳጣትና ጥቁር ቀለም ለመቀባት የትግሬን ሕዝብ እየጨፈጨፈ ደርግ እንዳደረገው አድርጎ ለውጪው ሕብረተሰብ ያቀርበው እንደነበረው ሁሉ አሁንም ኦብነግና ፤ ኦነግ በተመሳሳይ ትያትር  አይፈጽሙም  ለማለት ያዳግታል ፤ ይሄ አንዱና ተራው የፕሮፓጋንዳ ዘዴም እንደሆነ ከኛ ሊሰወር አይገባም ። ለግንጠላ ቡድኖችና ኢትዮጵያዊነትን ለሚጠሉ እንደወያኔ ኢትዮጵያን ለመበጣጠስ የተነሱ ሌላ የጠበቡ አሳዛኝ ፍጥረቶች የሚለቀሰው እንባ ከየት እንደመጣ ሊገባኝ አልቻለም ። ምነው ይሄንን እንደ ጥሩ የማይደርቅ ምንጭ የሚወርደው እንባችሁ ለእውነተኛ አገራችሁና ወገናችሁ ብታደርጉት ምንኛ በኮራንባችሁ ነበር ።

ከላይ እንደጠቀስኩት በኢትዮጵያ መፍረስና መበታተን ደንታ የሌላቸው እንዲያውም እንድትፈርስ ከፍተኛ ጥረት በሚያደርጉ በምዕራባውያንና በአረቦች ሚዲያ በሰፊው የሚዘገበው እውነት ለሰባዊነት ተቆርቅውሬ በመሆን እንዳልሆነ እንዴት ሚስጥር ሊሆንብን እንደቻለ ሳስበው እውን ያን ያክል ድፍን አርጎ ይሆን አምላክ የፈጠረን በማለት አያገባኝ ምርምር ውስጥ አገባለሁ ። እውን እውነተኛ ለሰብአዊነት ተቆርቋሪማ ከሆኑ ለምን በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል እየተካሄደ ያለውን ኢሰብአዊ ድርጊት አይዘግቡም? ሌላው በኢትዮጵያዊነቱ ስለሚያምን ይሆን? ግንጠላን ስላላቀነቀነ ይሆን? ከምርጫ 97 በፊትና ከምርጫ 97 አስከትሎስ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ወገናችን በእስር የሚማቅቅባት አገር አይደለችም እንዴ? መድረሻው ያልታወቀው ፤ በየ እለቱ እንደ ቅጠል የሚረግፈው ፤ ምነው ስለሱ አይዘገብም? የነሱን ድጋፍ ለማግኘት ጸረ ኢትዮጵያ መኮን አለበት ማለት ነው? እንደኔ ፤ እንደኔ ፤ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ሳይሆን ሁለቱም ጠላቶቼ ስለሆኑ "አህያ ላህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም" ብዬ ነው የማልፈው ።

ነገር ግን ይህንን ሁሉ ቀደም ብሎ ተረድቶ ለወያኔም ሆነ ለወያኔ አሳዳሪዎች ምዕራባውያን እንዲሁም በበረሃ ንዳድ አይምሯቸውን ለሳቱ ፤ የአባይ ወንዝ አዛዥነትን ለሚመኙ ሽርጣቸው እስኪጠልፋቸው ለሚቅበዘበዙ ሳያጎበድድ ፤ ወያኔንም በጠላትነት በመፈረጅ በተገኘው ሁሉ ተመቶ ከኢትዮጵያ ጫንቃ መውረድ አለበት ብሎ የሚታገለውን ታዲያ ለምን ጠላት በዛበት? ከወያኔ በበለጠ እንጂ ባላነሰ ጦር የሚወረወርበት ለምን ይሆን? የምክንያቱስ ምንጮች ከታወቀው ወያኔ ባሻገር ሌሎቹ እነማን ይሆኑ? ተገንጣዩ? አድርባዩ? የውጪው ኃይል? ኢትዮጵያን እንደናታቸው ጓዳ ሊቦጠቡጡ ያሰፈሰፉ? ግልጽ አልሆነልህ ብሎኛል እና መልሱን ካንባቢያን እተወዋለሁ ።

ድል በትግል !

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል ! !

ከብላቴን ጌታ መርቆሪዮስ